# ዴሞክራሲያ

**************************************************
* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) ልሳን*
**************************************************

ቅጽ 34 ልዩ ዕትም ግንቦት 2001 ዓ. ም.

## በኅብረት ትግል ወደ ድል

### በቂ ምላሽ ያላገኘ የትናንትናና የዛሬ ወቅታዊ ጥሪ

ጊዜና ሁኔታዎች በጋራ አድማ መትተው፤ የታሪክ ባለሃብት የሆነችው ሃገራችን ኢትዮጵያ በዚህ በቅርብ ጊዜ ታሪኳ፤ በዓለም ላይ የምትታወቀው በረሃብና በድህነት መሆኑ የሃቀኛ ዜጎቿን ቆሽት እንዳሳረረና እንዳበገነ ይኖራል። ለዘመናት በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ተንሰራፍተው የኖሩትን የካቻምናዎቹን ነገሥታት፣ ያምናዎቹን ጥቂት የደርግ መኮንኖችና የዛሬዎቹን እጅግ በጣም ጥቂት ኅጠኛ መሪ ተብዬዎች የሚያመሳስላቸው ዋነኛ ጉዳይ ቢኖር ሁሉም ሃገራችንንና ሕዝቧን ለአስከፊ ህይወት መዳረጋቸው ነው። በእውነትም ሦስትም አንድም ናቸው።

ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የዛሬው የኢትዮጵያችን ሁኔታ ደግሞ ይበልጥ አስፈሪ፤ ይበልጥ አሰቃቂና ይበልጥ አስጨናቂ እየሆነ መምጣቱ ሁላችንንም የነግ ከነገ በስቲያ ተስፋችንን ናፋቂ ማድረግ ብቻ ሳይሆን “ዛሬን እንዴት አድረን“ እያልን እንድንጨነቅ አድርጎናል። የውድ ሃገራችን የኢትዮጵያ የወቅቱ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታ በቅጡ ሲመረመር እያደር ከድጡ ወደ ማጡ ዓይነት መሆኑ ለሁሉም ገሃድ ሆኗል። የህወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት አራማጆች በሚቀርጿቸውና በሚከተሏቸው ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ሃገር ፖሊሲዎች ምክንያት ኢትዮጵያችን ዛሬ በዕድገት በመጨረሻ ተርታ ከሚሰለፉት የዓለም ሃገሮች አንዷ እንድትሆን ተገዳለች። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከምግብ ዕቃዎች ጀምሮ ሌሎችም የዕለት ተዕለት የመገልገያ ዕቃዎች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ንረት ተከስቶ ሕዝባችን እጅግ ዘግናኝ ለሆነ አሰቃቂ ኑሮ ተዳርጓል። በየጊዜው የሥራ አጡ ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ አብዛኛውን የሃገሪቱን ሕዝብ ለልመናና ለስደት መዳረግ ብቻ ሳይሆን ዜጎች በገዛ ሃገራቸው ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን ተስፋ አጨልሞታል። ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝባችን የሚተዳደርበት ግብርና መንግሥት ተብዬው በሚከተለው የተዛባ የመሬት ስሪትና የግብርና ፖሊሲ ምክንያት የምርት ማሽቆልቆል ደርሶበታል። የመሬት ስሪቱ ገበሬው የሚደክምበትን መሬት በባለቤትነት ለመያዝ እንዳይችል ከማድረጉም በላይ ያልተረጋጋ ሕይወት እንዲገፋ አስገድዶታል። በመሆኑም በምርት መዳበር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖን አሳድሯል። መንግሥት በፖሊሲና በተግባር ለመሬት አጠቃቀም፣ ለደን እንክብካቤ፣ ለመስኖ መስፋፋት፤ ለጎርፍ መከላከል፤ ለከብት ርቢና ሌሎችም ተዛማጅ

ጉዳዮች ዘላቂ ድጋፍና ትብብር ባለማድረጉ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የግብርናው መስክ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ በማሳደግ ረገድ ጉልህ ሚና የሚጫወትበት ሁኔታ የለም፡፡

የኢንዱስትሪው ዘርፍ እንደግብርናው ሁሉ ለሃገርና ለሕዝብ የረጅም ጊዜ ዘላቂ ጠቀሜታ እንዲውል ታስቦ ለእድገቱ በብርቱ የሚጣርለት ሳይሆን ይልቁንም ህወሓት/ኢሕአዴግ የማምረቻውን የማከፋፈያውንና የንግዱን መስክ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ያዋለበት፤ በውጤቱም የራሱንና የጋሻ ጃግሬዎቹን ጥቅም ያረጋገጠበት ድራማ ይፋ ከሆነ አሥራ ስምንተኛ ዓመቱን አስቆጥሯል፡፡ በሃገሪቱ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥም የህወሓት/ኢሕአዴግ ቀንደኛ መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው በሙስና እጅጉን ተዘፍቀው መገኘታቸው በየዕለቱ ይፋ እየሆነ ነው፡፡

በባንክ ብድር፤ በንግድ ፍቃድ፤ በንግድ ቦታ አሰጣጥ፤ በቀረጥ፤ በጨረታ አካሄድና አፈፃፀም ወዘተ ሂደቶች ፈጣሪ አድራጊዎቹ የህወሓት/ኢሕአዴግ ሹሞችና ካድሬዎቻቸው ሲሆኑ "የሌባ ዓይነ ደረቅ እንዲሉ" በሙስና የተዘፈቁቱ መልሰው ሌሎች ንፁሃንን የሚያንገላቱበት "ኮሚሽን" የተሰኘ አቋቁመው ለፍቶ አደሩን ሕዝብ በተለመደው የማመስና የማጎሳቆል ተግባራቸው ቀጥለዋል፡፡ ዛሬ በሃገራችን ውስጥ የመገልገያ መስኮች በሆኑት በባንክ፣ በኢንሹራንስ፣ በቱሪዝም፣ በቴሌኮሙኒኬሽን፣ በህንፃና በመዝናኛ ቦታዎች ግንባታ ዘርፎች ሊሟላ የሚገባው ቀዳሚ እቅድና ጥናት በበቂ ካለመከናወኑም በላይ ይህንኑ ሊፈፅሙ የሚችሉ የብቁ ባለሙያዎች እጥረት በጉልህ ይታያል፤ የብቁ ባለሙያ እጥረቱን የሚሞሉት ደግሞ ብቃቱም ችሎታውም የሌላቸው የሥርዓቱ ካድሬዎች መሆናቸው ህወሓት/ኢሕአዴግ ምን ያህል ለሃገርና ለሕዝብ ግዙፍ ጉዳዮች ፍፁም ግዴለሽ መሆኑን በግልፅ ያመለክታል፡፡

የሃገሪቱ ኢኮኖሚ በብርቱ የተዳከመና ይልቁንም በአብዛኛው በውጭ እርዳታና ብድር እየተንገዳገደና እየዳኸ ባለበት ባሁኑ ወቅት የሥርዓቱ ቁንጮዎች ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ኢኮኖሚው ከአሥራ አንድ በመቶ ነጥብ በላይ በየዓመቱ እያደገ በመሄድ ላይ ነው በማለት በአደባባይ እየዋሹ ነው፡፡ የአሥራ ስምንት ዓመታት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎቻቸው ሃገሪቱን ወደ ውድቀት እንጂ ወደ ዕድገት እንደማይወስዱ በቅጡ የተረዱት የህወሓት/ኢሕአዴግ ሹሞች ሰሞኑን በአዲስ ቅኝት የውድቀታቸው መንስዔ በቅርቡ በመከሰት ላይ ያለው የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ ነው እያሉ በተጨፈኑልኝ ላሞኛችሁ ዓይነት ሰበብ አስባብ በመደርደር ላይም ናቸው፡፡ ታሪክና ባንዲራን ከሚክድ መንግሥት የሐሰት ናዳ መዥጎድጎዱ የሚገርም ባይሆንም ሕዝብና ሃገር እየደማ እንዲቀጥል ግን ከቶውንም መፈቀድ የለበትም፡፡

ህወሓት/ኢሕአዴግ የሚያራምደው የፖለቲካ ሥርዓት ገና ሲፈጠር ከተለከፈበት የጠባብ ብሔረተኝነትና የጎጠኝነት በሽታ ዛሬም ድረስ ያልተላቀቀ፤ ለሥልጣኑ ማራዘሚያ ይበጀው ዘንድ ባለማቋረጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሃይማኖት፣ በዘርና በሌሎች ልዩ ልዩ ረቂቅ የመለያያ ዘዴዎች ለመበታተን ሌት ተቀን ከመድከም ፍፁም ያልተቆጠበ ፀረ-አንድነት ለመሆኑ ምስክር መጥራት አያሻም፡፡ የሕዝብ መብት የሚጠበቅበትና የሚከበርበት እያለ ዘወትር የሚፎለልበት ነገር ግን ራሱ ባሻው ጊዜና ወቅት መልሶ የሚሽረው የራሱ ብቻ የሆነ "ሕገ መንግሥት" ቀርፆ ባለማቋረጥ የኢትዮጵያውያንን ሰብዓዊ መብቶች ይጥሳል፤ ዛሬም ድረስ እንደልቡ ባፈቀደው ጊዜና ሰዓት በአደባባይ ከመግደል፤ ከማሰር፤ ከማንገላታትና ከማሳደድ ታቅቦ አያውቅም፡፡ ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለና በህወሓት/ኢሕአዴግ ቀጥተኛ ትዕዛዝና ተሳትፎ የሚደማው የሚቆስለውና የሚሞተው ሕዝባችን "የፍትኅ ያለህ!" እያለ ድምፁን ከፍ አድርጎ የድረሱልኝ ጥሪ በሚያሰማበት በአሁኑ ወቅት የህወሓት/ኢሕአዴግ ቁንጮዎች "አዲሶቹ የአፍሪካ ተስፋዎች" እየተባሉ በአንዳንድ የውጭ መንግሥታት መሞካሸታቸውና በልዩ ልዩ ዓለማቀፍ ጉባዔዎች ላይ ጎልተው እንዲታዩ መደረጉ ሌላው የዓለማችን አሳዛኝ ትዕይንት ነው፡፡ በዚህ ከተጨባጩና ከእውነቱ ፍፁም በራቀ ግምጋሜ የልብ ልብ የተሰማው ህወሓት/ኢሕአዴግም "እኔ ከሥልጣኔ ከተገለልሁ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች" እያለ

እስከማስፈራራት ደፍሯል፡፡ በበኩላችን ደግመን ደጋግመን ይህን ዓይነቱ ሁኔታና ሕዝብንና ሃገርን በቀጣይነት እንዲደማ ለአንዲትም ሰከንድ ቢሆን መፈቀድ የለበትም፤ በአስቸኳይ መቆም አለበት እንላለን፡፡ ይህ  ብሔራዊ ጥሪ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ጎልቶ መሰማት ያለበት ወቅትም ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው፡፡

በሌላ በኩል በሃገራችን ውስጥ በጉልበት በመግዛት ላይ የሚገኘው ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን በተለይ ለሃገር ዕድገትና ብልፅግና ወሳኝ ከሆኑ ኃይሎች ዋነኛውንና ቀዳሚውን የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ሆን ብሎ በረቀቀ ዘዴና ብልሃት በማዳከም ላይ መሆኑን ስናስተውል እጅግ መሪር በሆነ ጥልቅ ኃዘን ነው፡፡ ዛሬ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የትምህርት ዕድል ለመቋደስ የቻሉ ወጣቶች ሳይቀሩ በሃገራዊ ጉዳዮች ላይ በዘርና በጎሣ ለመከፋፈል እንዲችሉ ሥልጣን ላይ ባለው መንግሥት የሚደረግባቸው ግፊትና ጫና ዘግናኝ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ መንፈስን አጥፍቶ ጎጠኝነትን የሚያነግስ ብሎም ህወሓት ከደደቢት በረሃ ጀምሮ የኮተኮተውና በሃገራችን ዘርቶ ሊያበቅለው በብርቱ የሚደክምለት እኩይ ተልዕኮ አካል ነው፡፡ ከከፍተኛ ትምህርት  ተቋማት ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚመረቁ ተማሪዎች የህወሓት/ኢሕአዴግ አባል ለመሆን ፈቃደኛ ሲሆኑ ብቻ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ መደረጉም ሌላው የወቅቱ ተአምር  ሲሆን ሥርዓቱ ምንኛ በሕዝባችን ጫንቃ ላይ ተፈናጦ ለመቆየት የሚያልምና አድብቶ የሚሠራ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ታሪክ ራሱን ይደግማል ሆኖ ትናንት የደርግ ሥርዓት አራማጆች የሰደድ አባል ካልሆናችሁና በውይይት ክበብ ካልተሳተፋችሁ በሚል ወገኖቻችንን ያምሱበት የነበረውን ወቅትም ያስታውሰናል፡፡

በአሁኑ ወቅት ህወሓት/ኢሕአዴግ "የሚሊኒየም ግብ" በተሰኘ ፕሮግራም ትምህርት ቤቶች ለማሠራት በሚል ሰበብ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ገንዘብ በብድርና በድጋፍ ስም ለራሱ እያግበሰበሰ ከመሆኑም በላይ ፕሮግራሙን ወደተግባር ለመቀየር የሚከተላቸው ፖሊሲዎች እንደሌሎች ፖሊሲዎቹ ሁሉ በዘር ላይ የተመሠረቱ መሆናቸው ሥርዓቱ ምንኛ በጎጠኝነት ገመድ የተተበተበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን በህወሓት/ኢሕአዴግ የተቀረፀው የትምህርት ፖሊሲም የሃገራችን ወጣቶች በሥርዓቱ ከተወሰነላቸው ደረጃ በላይ እንዳይሄዱ የሚወስን፤ አዕምሯቸውን የሚያጠብና ነግ ከነገ በስቲያ ሊፈጠር የሚገባውን ሃገር ገንቢ ብቁ ዜጋ አምካኝ ፖሊሲ ነው፡፡  ትምህርትን ማቀድና በፖሊሲ መምራት የሃገርን የሰው ኃይል፣ የቁሳቁስና የገንዘብ አቅም ያገናዘበ፣ የሃገሪቱን የቋንቋዎች ሁኔታ በጥናት ላይ በተመሠረተ አስቀድሞ በሚገባ ጠንቅቆ ያወቀና የትናንትና የዛሬን የአንድ ሃገር ሕዝብ ታሪክ ከቁብ ያስገባ መሆን ሲኖርበት የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ለጊዜው በሥልጣን ላይ ሊያስቀዩዋቸው የሚችሉ መደለያ የሚሆኑ ጠባብና አካባቢያዊ አጀንዳዎችን ቀርፀው ተግባራዊ በማድረግ ለረጅም ዓመታት አንድነቷን ጠብቃ የኖረችውን ባለታሪክ ሃገራችንን ወደትናንሽ ጎጦች ለመበታተን አበክረው በመሥራት ላይ ናቸው፡፡ እንደሕዝባችን ጥንካሬና በመከባበር አብሮ የመኖር ፅኑ እምነት ባይሆን  ኖሮ የሃገራችን ዕጣ ፈንታ ዛሬ ሌላ በሆነ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነት ዋነኛ መከሰቻ ሆኖ ኢትዮጵያዊነት እስከዛሬ እንዲኖርና ለወደፊትም እንዲቀጥል ያስቻለው ይኸው የሕዝባችን ብልህነትና አርቆ አስተዋይነት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነት የዜግነት መለያችን ብቻ ሳይሆን ሃገራችን ለዘመናት አንድነቷ የተቋጨበት፤ በክፉና በደግ ወቅቶች ሕዝቧ ተደጋግፎ የቆመበት፤ የህልውናችን መሠረትና ምሰሶ እንዲሁም ሕዝባችን የተጋመደበት ጥብቅ ማተብ መሆኑን በተግባር ካስረገጥን ብቻ ነው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ሊቀጥሉ የሚችሉት፡፡ በምንም ዓይነት ጠባቦችና ዘረኞች ሕዝብና ሃገር እያደሙ እንዲቀጥሉ መፍቀድ የለብንም!!!

ህወሓት/ኢሕአዴግ በውስጥ በሃገራችን ሕዝብ ላይ ከሚያደርሰው የፖለቲካዊና የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ እንዲሁም ሳያሰልስ ከሚቀፈቅፋቸው የጎሣና የሃይማኖት ጥላቻዎችና ፍጥጫዎች በተጨማሪ ድንበር ዘልሎ በቅርቡ በጎረቤት ሃገር በሱማሊያ የውስጥ ጉዳይ ያደረገው ጣልቃገብነትና ያደረሰው ጭፍጨፋ ሃገራችንን ወደ ከፍተኛ አደጋ ገፍቷታል፡፡ ይህንን ሁኔታ ያጤኑ አካባቢያዊ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መንግሥታት ለሃገራችንንና

ለሕዝባችን ያንፀባረቁት ጥላቻም ነግ ከነገ በስቲያ ያልፋል ተብሎ ብቻ የሚተው አይደለም። በሻዕቢያ በኩል ዘወትር የሚገፋው የጥላቻና የጦርነት መንፈስም እንደቀጠለ እንጂ ከቶም አላባራም። የህወሓት/ኢህአዴግ ተከታታይ እኩይ ድርጊቶች ለሕዝባችን ጠላትን እንጂ ወዳጅን አላመረቱለትም። በሌላ በኩል ህወሓት/ኢሕአዴግ ከገዛ ሃገሩ ሕዝብ ይልቅ ለሌሎች የውጭ ዜጎች ተቆርቋሪ ነውና የሃገራችንን ለም መሬቶች ለሱዳን መንግሥት አሳልፎ በመስጠት ታላቅ የሃገር ክህደት ተግባርም ላይ በቀጥታ ተሳትፏል። እጅግ የሚያስደንቀው ይህን የገዛ ወገኑን በከፍተኛ ደረጃ የሚጨቁንን፤ የገዛ ሃገሩን በጎጥ ለመበታተን ጠንክሮ የሚሠራን፤ ከገዛ ወገኑ ይልቅ ለውጭ ዜጎች ጥቅም ጥብቅና የሚቆምንና አጎራባች ሃገሮችን ሳይቀር የሚያምስን ሥርዓት ለዴሞክራሲና ለፍትኅ ቆመናል የሚሉ እንደአሜሪካ ያሉ መንግሥታት በብርቱ ሲደግፉት መታየቱ ነው። በአሁኑ ወቅት እኒህንና የሃገራችንን ውስጣዊና ውጫዊ ወቅታዊ ሁኔታዎች በጥሞና ለምንከታተል ምንጫችን ውዲቷ ኢትዮጵያ የሆንን ሁሉ የችግራችን ዋነኛ ባለቤቶች፣ የገፈቱ ቀማሾችና መፍትሔዎቹ እኛና እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ መሆናችንን አጢነን ለተግባራዊ መፍትሄ በጋራ መነሳቱ አማራጭ የሌለው እጅግ አስቸኳይ ጉዳይ መሆኑን ልንስት አይገባም።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ከግንቦት ፲ እስከ ፱ ፪ ሺህ ፩ ዓ. ም ድረስ አምስተኛ ጉባዔውን ባካሄደበት ወቅት ቅድሚያ በመስጠትና ሰፊ ጊዜ በመውሰድ በሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በጥሞና መክሯል፤ ዘክሯል። አንኳር አንኳር ሃገራዊ ችግሮችን ከግንዛቤ ያስገቡ ውሳኔዎች አሳልፏል። መፍትሔዎችንም አመንጭቷል። ከሁሉም በፊት ሃገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ለደረሰችበት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድቀት፤ በዚሁም ሳቢያ ለህዝባችን እጅግ አሰቃቂ የኑሮ ሁኔታ መዳረግ፤ ያልተቋረጠ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች መጣስ፣ መንገላታት፣ መታሰር፣ መሰደድና መረሸን ዋነኛው ተጠያቂ ህወሓት/ኢሕአዴግ መሆኑን ምልዓተ-ጉባዔው በማያሻማ መንገድ በግልፅ አስረግጧል። ስለሆነም በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) እምነት ለሃገራችን የወደፊት ዕድገትና ብልፅግና እንዲሁም ለአዲሲቷ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ምሥረታ ይበጅ ዘንድ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥትና የፖለቲካ ሥርዓቱ መወገድ አለባቸው እንላለን።

የህወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት መወገድ አለበት ስንልም በምኞት ላይ የተመሠረተ አቋም ማንፀባረቅ ሳይሆን ይልቁንም ሃገራችን ዛሬ የምትገኝበትን ተጨባጭ ሁኔታ በበቂና እውነተኛ መረጃዎች ላይ በመመሥረት በጥልቀት በመገምገምና ወደፊት ለሚደረገው ትግል ስትራቴጂያዊ ግብ እንዲሆንና በሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ዘንድ ግልጥነትን እንዲያገኝ ለማስቻል ነው። በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) እምነት ህወሓት/ኢሕአዴግ እስካሁን በነቢብም ሆነ በግብር እንዳሳየው፣ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን በጎ የሚመኝና ሕዝቧንም በእኩልነት የሚመለከት አይደለም። ሥርዓቱ ሰላምና የተረጋጋ ኑሮን የማይሻ፤ ይልቁንም በሕዝብ መካከል መናቆርንና መከፋፈልን ሆን ብሎ የሚቀፈቅፍና የሚያበረታታ ነው። በኃይል ለሥልጣን የበቃ ነውና የሕዝብን ጥያቄ በኃይል የሚመልስ፤ በዚሁ ተፈጥሯዊ ባህርይው ምክንያትም በምርጫ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር የማያምን መሆኑን በግልፅ ያረጋገጠ ሥርዓት ነው። አልፎ አልፎ ዓለማቀፍ ደጋፊዎቹን ለማስደሰትና በዲፕሎማሲው መስክ የሚደረጉት ብርቱ ጥረቶች እያስገደዱት ብልጭ ድርግም የሚያደርጋቸውን የማታለያ ድርጊቶችን እየተመለከቱ የሥርዓቱን በጎነት ለመመስከር የሚዳዱ ቢኖሩ ከየዋህነታቸው ይታቀቡ ዘንድ ምክራችንን እንለግሳለን። በተቃዋሚ ጎራ ሆነው የዚህን የዋህ ምስክርነት ተግባር የሚጋሩ ቢኖሩ ግን የትግሉን አቅጣጫና ግብ እንደሳቱ ይቆጠራልና በዚሁ ጉዳይ ላይ ግልጥነትን ወደሚያስገኝ መድረክ ሊጋብዙን ወይም ልንጋብዛቸው ምንጊዜም ፈቃደኞች ነን። ለምሳሌ ህወሓት/ኢሕአዴግ የአምስት ዓመት ዕድሜ እየቆጠረ የሚመጣውንና እስካሁን ሙሉ በሙሉ በራሱ ፍቃድና ቁጥጥር ሥር ያደረገውን የማጭበርበሪያ ምርጫ ዳግም በ፪ ሺህ ፪ ዓ. ም. ለማካሄድ ሽር ጉድ እያለ ነው። በአፍ ጁዶ የተካነው የሥርዓቱ ቁንጮም “ከሥልጣኔ እወርዳለሁ“ የሚል ማጭበርበሪያ ወርውሮልን ይህንኑ እንደእውነት ይዞ ክርክር መግጠሙ ተጧጡፏል። “ከዝንጀሮ ቆንጆ…“ እንዲሉ ከህወሓት/ኢህአዴግ ሹማምንት መካከል የትኛው እንደሚሻል ማወዳደሩም ራሳችንን

ለከፍተኛ ትዝብት የሚጥል ብቻ ሳይሆን ወቅት እየጠበቁ በሚወረውሩልን አጀንዳዎች ላይ ዛሬም ጊዜ ማጥፋቱን ላለማቆማችን ግልፅ ምስክር ነው:: ይህ ጨርሶ መሆን የለበትም:: በአጭሩ ከሁሉም በፊት በህወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት መወገድ ላይ ብዥታ ሊኖር አይገባም እንላለን – ግልፅ ባልሆነ ግብ መተባበርም ከግቡ መድረስም አዳጋች ነውና::

ሌላው ግልፅነትን የሚሻ ጉዳይ በዋነኛው ግብ በህወሓት/ኢሕአዴግ መወገድ ላይ ማትኮር ያለበት በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገሮች የሚካሄደው ትግል የግድ መቀናጀት ያለበት መሆኑ ነው:: ካሁን በኋላ ለሚደረገው ትግል መሰጠት የሚገባውን ማናቸውንም ድጋፍ በቀጣይነት ማቅረብና ይህንኑ ሳያቋርጡ መቀጠልም የጨቋኙን ሥርዓት ፍፃሜ እንደሚያፋጥንና ከግባችንም በቶሎ እንደሚያደርሰን በፅኑ ከመተማመን ጋር ለተግባራዊነቱ በቁርጠኝነት ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል:: ከሃገር ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ለመክፈል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ዝግጁ እንዲሆኑና ሳያሰልሱ በቀጣይነት ተግባራዊ እንዲያደርጉ እንዲሁም የፖለቲካ፣ የሲቪክና የሙያ ድርጅቶች ትግላቸው በሃገር ውስጥ ከሚካሄደው ትግል ጋር እንዲቀናጅ ካልተደረገ ሁሌም የምንፈራው መጠላለፍ ደጋግሞ እየተከሰተ ትግሉን ባለህበት እርገጥ ማስኬድ ብቻ ሳይሆን የሕዝባችንንም የስቃይ ዘመን ማራዘሙ አይቀሬ ነው:: በውጭ ሃገሮች በዲፕሎማሲ መስክ እስከዛሬ ሲከናወኑ የቆዩ ተግባራት አበረታች መሆናቸው ባይካድም ለወደፊቱ ግን በአንድ ጊዜ በአንድ ድምፅና በአንድ ላይ የተቀነባበረ የጋራ ጥረት ማድረጉ የበለጠ ውጤታማ እንደሚያደርገን በመገንዘብ በጋራ ለሚቀነባበር ጥረት በጋራ መነሳቱ ከሚባክን አቅም ያድነናል፤ ለአመርቂ ውጤትም ያደርሰናል::

በሁለገብ የትግል ስልት የህወሓት/ኢሕአዴግን ሥርዓት ዕድሜ ለማሳጠር እንደሚቻል መተማመንንና የትግሉን ዘዴ የሚወስኑት የገዢው ቡድን ተከታታይ የኋላና የወደፊት ድርጊቶች እንዲሁም የህዝብ ፍላጎትና በቂ ዝግጅት መሆናቸው ምንጊዜም ሊዘነጉ አይገባም:: ሁለገብ የትግል ስልት ማንኛውንም የትግል ዘዴ አያበላልጥም ወይም አይኮንንም:: ማንኛውም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ዋነኛ ግብ የሆነውን የህወሓት/ኢሕአዴግን ሥርዓት ማስወገድን የሚያግዙ የትግል ስልቶች መጠቀም ሙሉ መብቱ ሲሆን ይህንኑ የሚያደርገው አስቀድሞ የራሱን ድርጅታዊ አቅምና ችሎታ አመዛዝኖ ነው:: አቅምና ችሎታውን አስመልክቶ ራሱን የዋሸ ተቃዋሚ ድርጅት ቢኖር የሚታገልለትን ሕዝብም ላለመዋሸቱ ምንም ዋስትና የለምና በሃቅ ለሃቅ ቆሞ ለአንዴና ለመጨረሻ የሕዝባችንን የዘመናት ስቃይና መከራ ልናቆም ወቅቱ የግድ ይለናል:: በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከራ ዘመን እንዲያበቃ የድርሻውን በማበርከት ላይ ላለ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ሁሉ ተገቢውን አክብሮታችንን የማንነፍግና ከሁሉም በላይ ለዘላቂ የትግል አጋርነት በሚያበቁን ተግባራት ላይ አበክረን ለመሥራት ብሎም በሂደት መተማመንን ገንብተን ወደታለመው የጋራ ግብ እንድናመራ ለሚያስችሉን ጉዳዮች ልዩ ትኩረት እንሰጣለን::

በኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) እምነት ስትራቴጂያዊ ግባችን የሆነውን የህወሓት/ኢሕአዴግ መወገድን እውን ለማድረግ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚከተሏቸው ታክቲካዊ የፖለቲካ ውሳኔዎችና እርምጃዎች በቀዳሚነት ሃገራችን ውስጥ በየዕለቱ የሚከሰቱትን ተጨባጭና ወቅታዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል:: ታክቲካዊ የፖለቲካ ውሳኔዎቹና እርምጃዎቹም በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ስምምነት የሚያስገኙም ሊሆኑ ይገባል:: ዛሬ ባለው የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንድ ድርጅት ብቻውን የሃገራችንን ግዙፍ ችግሮች ሊቀርፍ በጭራሽ አይቻለውም:: የብሔራዊ ነፃነታችንን ትግል በተሳካና ባስተማማኝ መልኩ ለማካሄድ፣ ለጥቆም የተረጋጋ የሽግግር መንግስት መስርቶ በዴሞክራሲያዊ መደላድሉ ላይ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ በማድረግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይሁንታ የሚያገኝ ዴሞክራሲያዊ መንግስት እንዲመሰረት በቅድሚያ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ኅብረት እውን ማድረግ ያስፈልጋል::

የኅብረት ምሥረታ ጥረት ለረጅም ጊዜ ተደጋግሞ ቢሞከርም ጥረቱ የረጅሙና የመራራው ትግል ታሪክ አካል ሆኖ በአዎንታዊ መልኩ መታየት ያለበት እንጂ ድክመታችንን ብቻ እያጋነኑ ማሳየት ለሚወዱና "ትግል ለምኔዎች" ሆነን ተሰላችተን እጅና እግራችንን አጣጥፈን ለህወሓት/ኢሕአዴግ ተገዢዎች ሆነን እንድንኖር ለሚመክሩን መሣሪያ ሆኖ ማገልገል የለበትም። እኛም በገዛ ሃገራችንና ወገናችን ላይ ተስፋ የቆረጥን ሆነን እንዳንታይ ደግመን ደጋግመን ማሰብና ይልቁንም የተቃዋሚዎች ኅብረት ምሥረታ ሳንሰለች አጥብቀን ልንታገልለት የሚገባ የችግሮቻችን መፍቻ ዋነኛው ቁልፍ መሆኑን ማመንና ማሳመን መቻል አለብን። እንሸፋፍነው ካላልን በስተቀር በዛሬይቱ ኢትዮጵያችን ውስጥ ጉልህ በሆነ መልኩ ከፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ጎልቶና ደምቆ የሌሎችን ድርጅቶች ሙሉ እምነትና ከበሬታ አግኝቶ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል የፖለቲካ ድርጅት የለም። በአንፃሩ በፀረ ህወሓት/ኢሕአዴግ ትግል የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማበርከት በሃቅ ከተሰለፈ የሌሎችን ከበሬታና አመኔታ የማያገኝ ድርጅትም አይኖርም። ወደፊት ሊፈጠር የሚገባው ኅብረት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል መኖር የነበረበትንና ያለበትን አመኔታና መከባበር ሊያስገኝ ይጠበቃል፤ በአመኔታና በከበሬታ ላይ የተመሠረተ ኅብረትም ዘላቂ የትግል አጋርነትን አጠንክሮ ወደታለመው ግብ ያደርሳል።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ወደፊት እውን የሚሆነው ኅብረት ሁሉንም ድርጅቶች አሰባሳቢ እንጂ አግላይ መሆን እንደሌለበት አጥብቆ ያምናል። የኅብረቱ የመሰባሰቢያ እምነቶችና የወደፊት ትልሞች በጋራ የሚቀረፁና የሚዳብሩ ቢሆኑም የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፣ ብሔራዊ ሉዓላዊነትና የሕዝቧ አንድነት መጠበቅ፣ ሁለንተናዊ የዜግነት መብቶች መከበርና የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት መወገድ መሠረታዊ የመሰባሰቢያ እምነቶች እንዲሆኑ አጥብቆ ይታገላል። እነኚህ መሠረታዊ እምነቶችም ከማንኛውም ድርጅት የፖለቲካ እምነት በላይ መሆናቸውን ይቀበላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፋታ በማይሰጥና ለዘመናት ባላቋረጠ የመከራና የስቃይ አዘቅት ውስጥ ስለሚገኝም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ ወይም በተናጥል በመነጋገርና በመቀራረብ በአስቸኳይ የኅብረት ምሥረታውን ሂደት እውን ማድረግ ስለሚጠበቅባቸው በዚህ በኩል የበኩሉን ለመወጣት ድርጅታችን ከፍተኛ ጥረት ከማድረግ አልተቆጠበም። አይቆጠብምም። በድርጅቶች መሀል ልዩነቶችንና ጥላቻዎችን የሚሰብኩ ተቃዋሚ መሳይ ድርጅቶች በተግባር ከህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ጋር የቆሙ የውስጥ ጠላቶች መሆናቸውን ከማጋለጥም ወደኋላ አይልም። ከዚሁ ጋር ኅብረትን ለመፍጠር እግራቸውን የሚጎትቱና ምክንያት የሚያበዙ ተቃዋሚ መሳይ ድርጅቶች በተግባር የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥትን እየረዱ መሆናቸውን ከማስገንዘብ ከቶም አንቦዝንም። በሕዝብና በሃገር ጉዳይ ይሉኝታና ለዘብተኝነት ጨርሶ ቦታ ሊኖራቸው አይገባም።

ሌላው መዘንጋት የሌለበት ዓቢይ ጉዳይ ኅብረቱ ከፖለቲካ ድርጅቶች ባሻገር ሃገር ወዳድ ዜጎችንንና የሲቪክ ማኅበረሰቦችንም እንዲያካትት ማድረጉ ትግሉን በሕዝባዊ ተሳትፎ ለማጀብ ማስቻሉ ነው። ኅብረቱ እውን እስኪሆንም በዋና ዋና ብሔራዊ ጉዳዮች ላይ ሰፋና ጠለቅ ያሉ ስብሰባዎች በማድረግ ምክክሮች ማድረግና በጥናት የተደገፉ ውይይቶች መክፈት ታላቅ ጠቀሜታ አለው። ህወሓት/ኢሕአዴግ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋሚ ንብረትና ቅርስ የሆነውን አንድነቱን በመሸርሸር ነው ነጣጥሎን በመግዛት ለረጅም ዓመታት የመቆየት ሕልሙን እውን ለማድረግ ሳይቦዝን የሚሠራው። ሕዝብ ባለማቋረጥ እየደማ እየቆሰለና እየሞተ ከሃገራዊና ብሔራዊ አጀንዳዎቻችን ለአፍታም ቢሆን ላለመዘናጋት ቃል ኪዳን መግባትና ለአንዴና ለመጨረሻ በኅብረት ትግል ለድል ለመብቃት እጅ ለእጅ መያያዝና ለተግባር መነሳት ያለብን ዛሬ ነው። እርስ በርስ መናከሱና መቧጨቁ አንዳችም እንዳልፈየደን የትናንት ታሪካችንን ገፆች ማገላበጡ በቂ ነው። በእርስ በርስ መናከስ የሚጠምዱንን በድፍረት ወግዱ ማለትና ለሚያቀራርቡንና በጋራ ሊያሰሩን ለሚችሉ ጉዳዮች ይበልጥ ትኩረት ለመስጠት ራሳችንን እናስገድድ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትንሳዔ ሊወለድ የሚችለው በኅብረት ትግል ለድል የበቃን እንደሆንና ለዚህ የትናንትናና የዛሬ ወቅታዊ ጥሪ በቂና ተግባራዊ ምላሽ የሰጠን እንደሆን ብቻ ነው።

**በተባበረ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!!!**
**የኅብረት ትግል ዋነኛው የወቅቱ ጥያቄ ነው!!!**
**እናቸንፋለን!!!**